# የአስተዳደር ውል

በአዲስ አበባ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ የሕግ ማርቀቅ፣ስርፀትና ምክር መስጠት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

**መግቢያ**

የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለህብረተሰቡ የሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች በዓይነትም ሆነ በስፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ መሆኑ ይታወቃል፡፡እነዚህን አገልግሎቶች ለማቅረብ መንግስት የተለያዩ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶችን በማቋቋም አገልግሎታቸውን ለህዝብ እንዲያቀርቡ እያደረገ ነው፡፡ እነዚህ የተቋቋሙ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች አገልግሎታቸውን ለማቅረብ የግብአት አቅርቦታቸው በሚፈለገው ልክ መሆን ይኖርበታል፡፡

የአስተዳር መስሪያ ቤቶች የሚያስልጓቸውን ዕቃዎች፣ግንባታዎች ወይም አገልግሎቶች በሕግ በተፈቀደው አግባብ ከሚያቀርብላቸው አካል ጋር ውል በመዋዋል እንዲያገኙ የሚያደርጋቸው አሰራር ተዘርግቷል፡፡ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ የመንግስትና የሕዝብ ሐብት ወጥቶ የሚፈለገው ግብአት ሳይገኝ የሚቀርበት ሁኔታ እንዳለ ለማየት ተችሏል፡፡በመሆኑም የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች የሚያደርጓቸው ውሎች የሚመራበት የአስተዳደር ውል ሕግ በተለይ የተደነገገ ቢሆንም በዚህ አግባብ ካለመሄድ የሚፈጠሩ ችግሮች መሆናቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም የአስተዳደር ውል ሕግ ምንነት በሚመለከት አጭር ግንዛቤ ሊፈጥር የሚችል ሰነድ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ይህ ሰነድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡በዚህ ሰነድ ውስጥ የአስተዳደር ውል መነሻ ምን እንደሆነና ከሌላው ውል በመን እንደሚለይ ለመግለጽ የተሞከረ ሲሆን የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ውስጥ ሲገባ በምን ሁኔታ እንደውሉ ማስፈጸም እንደሚችል ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡በመጨረሻም እንደውሉ ሳይፈጸም ሲቀር መውስድ የሚገባውን እርምጃ በተመለከተ ሕጉ ምን አማራጮችን እንዳስቀመጠ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡በመሆኑም የአስተዳደር ውል ሕግ ሰፋ ያለ ሲሆን ሁሉንም ጉዳዮች በዚህች አጭር ሰነድ ለመሸፈን ስለማይቻል ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት የተደረገ መሆኑ ከግንዛቤ ሊገባ ይገባል፡፡

## አስተዳደራዊ ውል

በአዳም ስሚዝ ፖሊቲካዊ ኢኮኖሚ ፍልስፍና መሰረት መንግስት ከገበያው በመውጣት ገበያው ራሱን በራሱ ማስተካከል ይችላል በማለት መንግስት ከገበያው በመውጣት በተለመደው የሠላምና ደህንነት ማስጠበቅ ስራ ላይ ትኩረቱን በማድረጉ ታላቁ የኢኮኖሚ ውድቀት ያጋጠመ መሆኑ ይታወቃል፡፡በመሆኑም መንግስት ከዚህ በመውጣት በተለይም በዋና ዋና አገልግሎቶች እንደ ትምህርት፣ጤና፣ውኃ፣መብራት፣ትራንስፖርትና የአካባቢ ንጽህና ስራዎች ላይ እንዲያተኩር የተደረገበትን ሁኔታ ለማየት ይቻላል፡፤በመሆኑም መንግስት እነዚህን አገልግሎቶች ለማቅረብ በአስተዳደር አካልነቱ ከሌሎች የግል ባለሀብቶች ጋር ውል በመግባት የሚያስፈልጉትን ግብአቶችና አገልግሎች ማግኘት ችሏል፡፡

የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ከሌላው ተዋዋይ ወገን ጋር የሚያደርጓቸው ውሎች ከማናቸውም ሌሎች ውሎች ተለይተው የሚታዩ ናቸው፡፡በአገራችን ያለውን ሁኔታ የተመለከትን እንደሆነ በፍትሐብሄር ህጋችን ቁጥር 1675(2) ላይ በግልጽ እንደተመለከተው እነዚህን ጠቅላላ ደንቦች የሚለውጡ ወይም የሚያሟሉ ስለ አንዳንድ ውሎች የተጻፉ ልዩ የሆኑ ደንቦች በዚህ ሕግ በ5ኛው መጽሐፍና በንግድ ሕግ ውስጥ ተመልክተዋል ይላል፡፡ስለሆነም ማናቸውም ውሎች ስለ ውሎች በጠቅላላ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት የሚመሩ ሲሆን የአስተዳደር ውሎች ግን ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ድንጋጌ መሰረት ይመራሉ፡፡እነዚህ ድንጋጌዎችም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3131 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች መሰረት የሚመሩ ይሆናል፡፡

## የመንግስት ህጋዊ ሰውነት

መንግስት ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 394 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡መንግስት በስሩ በሚገኙት መስሪያ ቤቶች አማካይነት በሕግ የተሰጠውን መብቶቹን ሊጠቀምባቸው የሚችል ስለመሆኑም ተመልክቷል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ህጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት በመሆናቸው መብትና ግዴታ ያላቸው መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 397 በግልጽ ደንግጓል፡፡ስለሆነም እነዚህ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች በሚቋቋሙባቸው ዓዋጆች እስከተቋቋሙ ድረስ የመንግስት አካላት ናቸው ማለት ነው፡፡ስለሆነም እነዚህ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ሌሎች ሕጋዊ መብቶቻቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ውል የመዋዋል ዕጋዊ መብት ያላቸው መሆኑን በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## የአስተዳደር ውል ከሌሎች ውሎች በምን ይለያል?

የአስተዳደር ውል የሚያደርገው የመንግስት ተቋም ለህዝብ ጥቅም የሚያደርገው ውል ነው ተብሎ ይገመታል፡፡በመሆኑም የህዝብ ጥቅም ከተዋዋይ ወገን ጥቅም ይልቅ ከፍ ያለ ግምት

ይሰጠዋል፡፡ለዚህም ሲባል አንዳንዴ መርህ የሚጣስበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ለምሳሌ ሁለት ወገኖች አንድን ጉዳይ ለመፈጸም ወይም ላለመፈጸም ስምምነት ሲያደርጉ እነዚህ ተዋዋዮች እኩል መሆናቸው የመርህ ጉዳይ ነው፡፡በአስተዳደር ውል ግን የአስተዳደር መስሪያ ቤቱና ተዋዋዩ ወገን እኩል አይደሉም፡፡ይህ መርህ መጣስ ነው፡፡በኮመን ሎው የህግ ስርዓት መሰረት ግን ሁሉም የውል ዓይነቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው ተዋዋይ ወገኖች ውሉን በተመለከተ ጉዳይ እኩል ሲሆኑ ልዩነት አላቸው የሚለው አስተሳሳብ ያለው ግን በሲቪል ሎው የህግ ስርዓት መሰረት ነው፡፡በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ የሲቪል ሎው የሕግ ስርዓት ተከታይ አገር እንደ መሆኗ መጠን ይህ ልዩነት በአስተዳደር ሕጋችን ውስጥ ይንጸባረቃል፡፡

እንዲህ ከሆነ ታዲያ አስተዳደራዊ ውል ምንድነው?

በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1675 ላይ የተገለጸው የውል ትርጉም ለአስተዳደራዊ ውል የሚያገለግል ሆኖ ነገር ግን በተጨማሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3132 ላይ የተመለከተውንም ይጨምራል፡፡በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1675 መሰረት ውል ማለት ንብረታቸውን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግኑኝነት በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው ብሎ ይደነግጋል፡፡ከዚህ የምንረዳው በመርህ ደረጃ ሁለቱ ግዴታ የሚገቡ ወገኖች እኩል ደረጃ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡በፍ/ብ ሕ/ቁጥር 3132 ላይ ያለውን ስንመለከት ደግሞ አንድ ውል እንደ አስተዳደር መሥሪያ ቤት ውል ሆኖ የሚቆጠረው

ሀ/ ሕግ ወይም ተዋዋዮቹ ግልጽ በሆነ ቃል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ነው ያሉት ሲሆን፤

ለ/ ውሉ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር የተያያዘና ለሥራውም አፈጻጸም የተዋዋዩን የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱን የሥራ ተካፋይነት ሳይቋረጥ የሚጠይቅ ሲሆን፤

ሐ/ በውሉ ውስጥ ለጠቅላላ ጥቅም አስቸኳይ በመሆናቸው ብቻና የግል ሰዎች በሚያደርጓቸው ውሎች ውስጥ የማይገኙ አንድ ወይም ብዙ ውለታዎች ያሉበት ሲሆን ነው ይላል፡፡

እዚህ አንቀጽ ላይ የተቀመጡት የህዝብ አገልግሎት ሥራ የሚለው ኃረግ ራሱ ምን ማለት እንደሆነ ከፍ/ሕ/ቁጥር 3207 እና 3244 መረዳት ይኖርብናል፡፡በዚህም መሰረት አንድ የህዝብ አገልግሎት ሥራ የሚባለው ይኸን ሥራ የግል የሆነ ድርጅት በሚገባ ለማካሄድ የማይችለው ነው ብሎ ወስኖ በጠቅላላ ለህዝቡ አስፈላጊነት ያለው ነው በማለት ራሱ የሚያካሂደው ነው በማለት ያስቀምጣል፡፡በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አደረጃጀት በማቋቋሚያ ዓዋጅ አማካይነት አዲስ መስሪያ ቤቶች ሲቋቋሙ ወይም ሲፈርሱ እንመለከታልን፡፡ይህ የሚሆነው የግሉ ሴክተር የማይገባባቸውና መንግስት ወደ ገበያው በመግባት አገልግሎቱን ማቅረብ ሲያስፈልገው መስሪያ ቤት የሚያቋቁምለት ወይም ተቀራራቢ ስራ እየሰራ ነው ለሚለው መሥሪያ ቤት አገልግሎቱን

እንዲሰጥ በማድረግ የግሉ ዘርፍ ሊያቀርብ ያልቻለውን የሚያቀርብበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ስለሆነም የህዝብ አገልግሎት ተብሎ የሚወሰደው የግሉ ዘርፍ የማያቀርባቸው ሆነው መንግስት ራሱ ለማቅረብ የሚወስናቸው አገልግሎቶች ናቸው፡፡እዚህ ላይ የግሉ ዘርፍ ቢያቀርባቸውም በሚፈለገው መጠንና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከገበያው ላይ አገልግሎቶችን ለማግኘት አቅም አይኖራቸውም ተብለው ለሚታሰቡ የህብረተሰብ ክፍሎች መንግስት ራሱ የሚያቀርብበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል መዘንጋት የለበትም፡፡

ከላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3132(1) ላይ ለማየት እንደተሞከረው ተዋዋይ ወገኖች ውሉ የአስተዳደር ውል ነው ሲሉ በግልጽ የተናገሩት መሆን እንደሚኖርበት መደንገጉን ነው፡፡እዚህ ላይ መታየት ያለበት ማናቸውም ተዋዋዮች ይህ ውል አስተዳደራዊ ውል ነው ስላሉ ብቻ አስተዳደራዊ ውል ሊሆን አይችልም፡፡ሌሎች ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አንድ ውል አስተዳደራዊ ውል እንዲሆን የግድ አንደኛው ተዋዋይ ወገን የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ሊሆን ይገባዋል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ አንደኛው ተዋዋይ ወገን የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ስለሆነና ተዋዋዮቹ ይህ ውል አስተዳደራዊ ውል ነው ብለው ስለጠሩት አስተዳደራዊ ውል ይሆናል ወይ የሚለውንም ስንመለከት ሁለቱ ወገኖች ውል ውስጥ የሚገቡበት ጉዳይ የህዝብ አገልግሎት ሊሆን ይገባዋል፡፡የህዝብ አገልግሎት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ደግሞ ከፍ ብለን አይተናል፡፡ስለሆነም አንድ የአስተዳደር ውል የአስተዳደር ውል እንዲሆን ካስፈለገ እነዚህን ነጥቦች መሟላት ይገባቸዋል ማለት ነው፡፡

እስከአሁን ስንመለከት የቆየነው አንድን አስተዳደራዊ ውል ለመመስረት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሲሆን የውሉን ይዘት በተመለከተ ምን መሆን እንደሚገባው ከዚህ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን፡፡

**የውሉ ጉዳይ**

የውሉጉዳይውሉአስተዳደራዊ ውል መሆኑን እና ያለመሆኑን ለመለየት ይጠቅማል፡፡በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3207(1) ላይ እንደተመለከተው ሁለት ምክንያቶች ማንኛውም ስራ የህዝብ አገልግሎት እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡አንዱ ምክንያት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊነቱ የታመነበት እንደሆነ ነው፡፡ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ይህ ለአጠቃላይ ጥቅም አስፈላጊ ነው የተባለው ጉዳይ በተለያዩ ምክንያቶች የግሉ ዘርፍ በራሱ ተነሳሽነት ሊገባባቸው የማይፈልጋቸው ናቸው፡፡ስለሆነም የውሉ ጉዳይ እነዚህ አሟልቶ ሲገኝና ከተዋዋይ ወገኖች አንደኛው የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ሲሆን ውሉ የአስተዳደር ውል ይሆናል፡፡

የተዋዋዩን ተካፋይነት ሳይቋረጥ የሚፈልግ መሆንን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3132(ለ) ላይ ያለውን ስንመለከት ተዋዋዩ ወገን እድሜ ልኩን ከአስተዳደሩ መሥሪ ቤት ጋር የሚያቆራኘው ሳይሆን

ሥራው ሳይቆራረጥ፣ተከታታይነቱ ሳይረበሽ ስራው እንዲከናወን የሚያስፈልግ መሆኑን ለመግለጽ የተቀመጠ መሆኑን መረዳት ይገባናል፡፡

የውል ግዴታ ውስጥ ለመግባት የሚፈልጉ ተዋዋይ ወገኖች እንደፈለጉ የሚዋዋላቸውን አካል ለመምረጥ ሙሉ መብት አላቸው፡፡የአስተዳደር ውል ውስጥ የሚገባ የመንግስት መስሪያ ቤት ግን እንደፈለገው ሊመርጥ አይችልም፡፡ውል ውስጥ የሚገባበት ሀብት የመንግስትና የሕዝብ በተለይም ከግብር ከፋዩ የሚሰበሰብ ገንዘብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተገቢው የሚፈለገውን ያህል ጥቅም እንዲያስገኝ ለማድረግ ሲባል ፍትሃዊና ግልጽነት ባለው መንገድ በጨረታ ሂደት አሸናፊ በመለየት የሚከናወን ይሆናል፡፡ይህንን ሁኔታ ከዓዋጅ ቁጥር 649/2001 መግቢያ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዢና ንብረት አስተዳደር ዓዋጀወ ቁጥር 17/2002 አንቀጽ 5(1) ለመረዳት ይቻላል፡፡ በዓዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 2/5 መሰረት ግዢ ማለት ዕቃዎችን፣የግንባታ ዘርፍ ሥራችን፣እና አገልግሎቶችን በግዢ፣በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ይህ ማለት በአዋጁ አንቀጽ 33 ላይ በተቀመጡት የግዢ ዘዴዎች መሰረት በቅደም ተከተል መፈጸም የሚገባ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ስለሆነም ከመንግስት መስሪያ ቤት አንጻር በፈለገው ሁኔታ ተዋዋዩን የሚመርጥበት ሳይሆን በህግ በተቀመጠው አግባብ የተሻለ ጥቅም ለህዝብ ከሚሰጠው ጋር የሚዋዋል መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

## የአስተዳደር ውል ውጤት

አንድ የአስተዳደር ውል መፈጸም በውሉ ውስጥ የገባውን ተዋዋይ ግዴታ የሚያስቀርለት ይሆናል፡፡ውሉ እስከተፈጸመ ድረስ ተዋዋይ ወገኖች ላይ እንደ ሕግ የሚቆጠርና አስገዳጅ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731/1 በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ማንኛውም ውል የግድ በተዋዋይ ባለዕዳ መፈጸም ያለበት ካልሆነ በስተቀር ስለተዋዋዩ ባለዕዳ በመሆን ሌላ 3ኛ ወገን ሊፈጽመው የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1740(1) ላይ ተመልክቷል፡፡የአስተዳደር ውልን በተመለከተ ግን ራሱ የተዋዋለው ወገን የሚፈለግበትን ግዴታ መወጣት የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር3172/1/ ደንግጎ እናገኛለን፡፡ በአገራችን የመንግስት መስሪያ ቤቶች የተሻለ ብቃትና አቅም ያለው ኮንትራክተር በጨረታ ተወዳድሮ አሸናፊ ከሆነ በኋላ ከፊል ስራዎችን ለሌላ ኮንትራክተር በመስጠት ስራዎች የሚሰሩበት ሁኔታ ያለ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3201 እስከ 3206 በተመለከተው መሰረት ስራውን ለሌላ አካል መስጠት የሚቻል ቢሆንም አስቀድሞ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ሊፈቅድ የሚገባው መሆኑ ተመልክቷል፡፡እየሆነ ያለው ይህ ነው ወይ?

## የአስተዳደር ውል አጠቃላይ ፖሊሲ

በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3177(1) ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ከአስተዳደር መስሪያ ቤት ጋር የተዋዋለ ወገን የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ግዴታውን ያለ መወጣቱ ስራውን እንዲያከናውን የማያስችለው ካልሆነ በስተቀር መስሪያ ቤቱ ግዴታውን ሳይወጣ በመቅረቱ ብቻ በእርሱ በኩል ያለበትን ግዴታ አልፈጽምም ለማለት የማይችል መሆኑ ተደንግጓል፡፡ከዚህ አንጻር በዋናው የውል ሕግ ተዋዋይ ወገን አስቀድሞ ከባለገንዘቡ ሊፈጸም የሚገባው ጉዳይ ካለ መፈጸሙን ባለዕዳው ማረጋገጥ የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1757 ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ውሉ የአስተዳር ውል ከሆነ ግን ተዋዋዩ በእርሱ በኩል ያለውን ግዴታ አልፈጽምም ማለት የማይችል መሆኑ በሚገባ መታወቅ አለበት፡፡ይህ ሊሆን የቻለው የአስተዳደር ውል በባህሪው ለብዙኃን ጥቅም ሲባል የሚገባ ግዴታ በመሆኑ ይህ የብዙኃን ጥቅም አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ሲባል የሚደረግ የሕግ ጥበቃ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

### የአስተዳደር ውል በግድ ስለማስፈጸም (3194)

ውልን በግዴታ ማስፈጸም በባህሪው ባለዕዳውን በውሉ ላይ በተመለከተው መሰረት ራሱ ግዴታውን እንዲወጣ ማድረግ ነው፡፡ከዚህ አንጻር የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ግዴታውን እንዲፈጽም ዳኞች ሊያስገድዱት እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3194 ላይ በግልጽ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ይሁን እንጂ ተዋዋዩ ወገን የሚደርስበት ኪሳራ ካለ ግን የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ሊከፍል እንደሚችል በዚሁ አንቀጽ ላይ ተመልክቷል፡፡

### እንደገና በጨረታ ለሌላ ስለመስጠት

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3291 መሰረት የአስተዳር ውል የተሰረዘ እንደሆነ የአስተዳር መስሪያ ቤቱ ቀሪ ስራዎችን እንደገና ጨረታ በማውጣት አወዳድሮ ለአሸናፊ በመስጠት ወይም ደግሞ በስምምነት ለሌላ ተዋዋይ በመስጠት ማሰራት የሚችል መሆኑ ተመልክቷል፡፡ይሁን እንጂ አዲስ ዋጋ በመሰጠቱ ምክንያት ተጨማሪ ወጪ አስከትሎ እንደሆነ ኪሳራውን የመጀመሪያው ተዋዋይ ወገን የሚከፍል መሆኑ ጭምር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የመንግስት ስራዎች በውሉ መሰረት ባለመከናወኑ በመንግስት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በመቀነስ መፍትሄ ለመስጠት ውሉን ማቋረጥ የተሻለው መፍትሄ ሆኖ ከተገኘ ወዲያውኑ ስራውን በሌላ አካል በማስቀጠል ለፍጻሜ ማብቃት ይገባል፡፡

### የአስተዳደር ውል ስለማቋረጥ እና ስለማፍረስ

የአስተዳደር መስሪያ ቤት የገባቸው ውሎች ለህዝባዊ አገልግሎት የማይጠቅም መሆኑ ከታመነበት የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 3180 ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡በውል ማቋረጥና ውል ማፍረስ መካከል ሰፊ ልዩነት ያለ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ውል ማፍረስ በእንግሊዝኛው cacellation ማለት ሲሆን ውል ማቋረጥ ደግሞ termination ማለት ናቸው፡፡ ስለሆነም ውል ማፍረስ ተዋዋይ ወገን የሆነው እንደውሉ መፈጸም

ባለመቻሉ የሚደረግ ሲሆን ውል ማቋረጥ ደግሞ የተዋዋይ ወገን ጥፋት ሳይኖር በውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት ግዴታ መፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ የሚፈጸም ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ የአስተዳደር ውል ስለሚፈርስበት ሁኔታ ያለው የለም፡፡በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1676(1) መሰረት በውል ጠቅላላ ሕጉ የሚመራ ይሆናል፡፡በዚህም መሰረት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1784 መሰረት በፍርድ ቤት ውሉን ለማፍረስ ይቻላል፡፡ውልን ማቋረጥ በተመለከተ ግን የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ በራሱ ውሉን ለማቋረጥ ያልተገደበ መብት ያለው መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡እንደዚህ በሆነ ጊዜ ግን ምንም ጥፋት የሌለበት ተዋዋይ ወገን የደረሰበትን ኪሳራ መካስ የሚገባ መሆኑ መረሳት የለበትም፡፡

## የአስተዳደር ውል ስለማሻሻል

የአስተዳደር ውልን በተናጠል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ማሻሻል የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3283(1) ላይ ተመልክቶ እናገኛለን፡፡ተዋዋይ ወገን ለመቃወም የሚችለው የሚደረገው ማሻሻል ለህዝብ ጥቅም ሲባል ካልሆነና በወጪ ደረጃ ተዋዋዩን የሚጎዳው እንደሆነ ብቻ መሆኑን በዚሁ የህግ ቁጥር ንዑስ 1 እና 2 ላይ ተመልክቷል፡፡ከተዋዋዮች መብት አንጻር ስንመለከተው በሌላ ውል ተዋዋዮች እኩል በመሆናቸው የሁለቱንም ስምምነት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡የአስተዳደር ውል ግን በባህሪው ተዋዋዮቹ በእኩል ደረጃ ላይ የሚገኙ ባለመሆኑ የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ባሻሻለው ውል ተዋዋዩ የሚገደድ ይሆናል፡፡

## የአስተዳደር መስሪያ ቤት መብት

የአስተዳደር መስሪያ ቤት በሕግ የተሰጡት ሁለት መብቶች ይኖሩታል፡፡የመጀመሪያው ስራውን የመምራት መብት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስራውን የመቆጣጠር መብት ነው፡፡በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3250(1) መሰረት የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ስራውን ለመቆጣጠር እንደሚችል በግልጽ ተቀምጧል፡፤የአስተዳደር አካሉ ተወካዮች ተዋዋዩ የሚያከናውናቸው ስራዎችን ቦታው ድረስ በመገኘት የመቆጣጠር ስራ ሊያሰራ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3251(1) ላይ ተመልክቷል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ተዋዋዩ የሚያከናውናቸው ስራዎች በሚፈልጋቸው መንገድ እንዲሆኑለት ለማድረግ ስራውን የመምራት መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3252 ላይ ተመልክቷል፡፡እነዚህ የአስተዳደር መስሪያ ቤት መብቶች ያስፈለጉበት ምክንያት በውሉ መሰረት እንዲፈጸም ውል ውስጥ የተገባበት ጉዳይ የህዝብ የአስተዳደር ስራ ጉዳይ ናቸው፡፡እየተከናወኑ የሚገኙት ደግሞ በመንግስት ሀብት ነው፡፡ስለሆነም በህዝብ በመብትና ጥቅም ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ከወዲሁ ለመቀነስ ሲባል ተዋዋይ የሆነው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ተዋዋዩ ስራውን በውሉ መስረት እያከናወነ መሆኑን መቆጣጠር ሲሆን አለፍ ሲልም ስራውን በበላይት በመምራት ከዳር ለማድረስ የሚሰራ ይሆናል፡፡

## ስለ ስራዎች ርክክብ

ከዚህ በላይ በተመለከተው አግባብ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ሥራውን እየመራና እየተቆጣጣረ በውሉ መሰረት ተዋዋዩ ግዴታውን ከፈጸመ ቀጥሎ የሚመጣው ነገር ርክክብ ማድረግ ነው፡፡በፍ/ሕ/ቁጥር 3274 መሰረት የመጀመሪያ ርክክብ ሲደረግ የተሰራው ስራ እና የጎደለ ተለይቶ በመመዝገብ ይሆናል፡፡ይሁን እንጂ ተዋዋዩ የሥራውን ሁኔታ በመለዋወጥ የሰራቸውን ነገሮች ለጊዜው መረከብ ማለት በዝምታ እንደመቀበል የሚቆጥር ስለሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ከዚያ ውጪ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ የጎደሉ ነገሮችን ለይቶ በመመዝገብ ለጊዜው መረከቡ ተዋዋዩ እነዚህን የጎደሉ ነገሮች በራሱ ወጪ የማሟላት ግዴታ የሚጥበልት ነው የሚሆነው፡፡አብዛኛውን ጊዜ የሚታየው የመጀመሪያ ደረጃ ርክክብ ከተደረገ በኋላ መስተካከል የሚገባቸው ነገሮች ተስተካክለው የመጨረሻ ርክክብ ከመደረጉ በፊት የተሰራው ስራ አገልግሎት ላይ ስለሚውል ቀሪ ስራዎች ላይ ባለመግባባት ለክርክር የሚዳርግ ይሆናል፡፡ስለሆነም ተዋዋይ የጎደሉት በአፋጣኝ እንዲያሟላ ማድረግ ወይም እርሱ ሊያሟላው ካልቻለ በእርሱ ኪሳራ ሌላ ተዋዋይ እንዲያሟላው በማድረግ ስራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

## የአስተዳደር ውልና የግልግል ዳኝነት

አብዛኛውን ጊዜ የአስተዳደር ውሎች ላይ በተዋዋዮች መካከል በውል አፈጻጸም ሂደት መግባባት ሳይኖር ሲቀር በፍርድ ቤት ከሚደረግ ክስ ሂደት በፊት በግልግል ዳኝነት ጉዳያቸውን በማየት መፍትሄ ለመስጠት ስምምነት ሲያደርጉ ይታያል፡፡የፍትሐብሄር ሕጋችን ከቁጥር 3307 ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ቁጥሮች ስለግልግል ደንግጎ ይገኛል፡፡በፍ/ሕ/ቁጥር 3307 ላይ እንደተመለከተው ግልግል ማለት ተዋዋይ ወገኖች አንዱ ላንዱ አንድ ነገር ትቶ ወይም ሰጥቶ የተጀመረውን ክርክር የሚያቆሙበት ወይም የሚፈጠረውን ክርክር አስቀድመው የሚያስቀሩበት አንድ ውል ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 315(2) በግልግል እንዳይወሰን በሕግ የተከለከለ ጉዳይ ወይም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3131 እንደተነገረው ያለ ጉዳይ ሲሆን ለግልግል ዳኝነት አይቀርብም በማለት ደንግጓል፡፡በዚህ ጉዳይ ላይ የሕግ ባለሙያዎች በሀሳብ የተለያዩበትን ሁኔታ መመልከት ይቻላል፡፡ተዋዋይ ወገኖች በውላቸው ላይ እስካስቀመጡት ድረስ ህግ ነውና በውላቸው መሰረት መፈጸም አለበት የሚሉና ዋናው የፍትሐብሄር ሕግ ላይ የአስተዳደር ውሎች በግልግል ጉዳያቸው አይታይም በማለት ባያስቀምጥም በኋላ የወጣው የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የከለከለ በመሆኑ በግልግል መታየት የለበትም በማለት ይከራከራሉ፡፡የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ውሳኔ ቅጽ 7 በሰበር መዝገብ ቁጥር 27349 በብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና በአማራ ክልል ዘላቂ ግብርና ተሃድሶ ኮሚሽን መካከል ባለው ክርክር በተዋዋዮች መካከል ባለው ውል መሰረት በግልግል መታየት ያለበት በመሆኑ በፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ በመቃወሚያ መዘጋቱ በአግባቡ ነው በማለት የከፍተኛ

ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡ስለሆነም የተሻለ የሚሆነው ከመጀመሪያው የውሉ አካል እንዳይሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**የአስተዳደር ውል ከዓዋጅ ቁጥር 17/2003 አንጻር**

የግገርና ንብረት ማስወገድ ዓዋጅ ቁጥር 17/2003 አንቀጽ 18 መሰረት በመንግስት መስሪያ ቤቶችና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግኑኝነቶች በጽሁፍ መደረግ አለባቸው ፡፡በጽሁፍ ያልተደረጉ ማናቸውም ግኑኝነቶች በመከታተል በጽሁፍ መረጋገጥ አለባቸው በማለት ይደነግጋል፡፡እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1724 መሰረት በጽሁፍ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡አንዳንድ ጊዜ አስቸኳይ በማለት በቃል በሚደረጉ ውሎች ወዲያው በጽሁፍ ማረጋገጥ ባለመቻሉ ተዋዋዮች በታዘዝነው መሰረት ብንፈጽምም ክፍያ ሊፈጸምልን አልቻለም በማለት ሲያማርሩ የሚታዩና ጉዳዩም ሊፈታ ባለመቻሉ የመልካም አስተዳደር ችግር ሲሆን ይስተዋላል፡፡

የመንግስት ግገር ዘዴዎች ግልጽ ጨረታ፤በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈጸም ግገር፣ በዋጋ ማቅረቢያ፣በውስን ጨረታ፣ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግገር እና በሁለት ደረጃ የሚፈጸም ግገር መሆኑን በዓዋጁ አንቀጽ 25(1) ላይ በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡በአማራጭ ደረጃ ከሁሉም ዘዴዎች በዚሁ ዓዋጅ ካልተፈቀደ በስተቀር ግገሩው የሚፈጸመው በግልጽ ጨረታ ስለመሆኑ በንዑስ 2 ላይ ተመልክቷል፡፡ይህም ማለት ሌሎቹ የግገር ዘዴዎች በግልጽጨረታ ለመግዛት ያልተቻለ እንደሆነ በአማራጭነት የተቀመጡ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡በጨረታ አሸናፊ የሚሆነው ተወዳዳሪ በውሉ መሰረት የማይፈጽምበት ሁኔታ ቢኖር ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚሆን የውል ማስከበሪያ ለተዋዋይ መስሪያ ቤቱ መስጠት የሚገባው ስለመሆኑ በዓዋጁ አንቀጽ 39 ላይ የተደነገገ ሲሆን ተዋዋዩ ውሉ ከተፈረመ በኋላ የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጠው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እንደሆነና ይህ የቅድሚያ ክፍያ ሊፈጸም የሚችለው ደግሞ ተዋዋዩ የሚወስደው ቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ መጠን ያህል ዋስትና ሲያቀርብ መሆኑን በዓዋጁ አንቀጽ 40 ተመልክቷል፡፡አብዛኛውን ጊዜ ተዋዋዮች ቅድሚያ ክፍያ ተቀብለው እንደውሉ መፈጸም ሳይችሉ የሚጠፉበት ሁኔታ የሚታይ ሲሆን የመንግስት ሀብት ተመላሽ ለማድረግ የፍትሐብሄር ክስ ለማቅረብ አስተዳደሩ ሲገደድ ይታያል፡፡

**ማጠቃለያ**

የአስተዳደር ውል እንደማናቸውም ውል ግዴታ የሚገባበት ውል በመሆኑ ውሉ ከሚረቀቅበት ጊዜ ጀምሮ ውሉ እስኪፈጸም ድረስ ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡የአስተዳደር ውል የሕዝብ መብትና ጥቅም በሰፊው ያለበት ጉዳይ በመሆኑ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ እንደውሉ እንዲፈጸምለት ለማድረግ ሕጉ ወደ አስተዳደር መስሪያ ቤቱ ያደላ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ

ነው፡፡ስለሆነም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውል ሲገቡ ሕጉ በተለይ የሰጣቸውን መብት በመጠቀም ተዋዋዩ ወገን ግዴታውን እንዲፈጽም ማድረግ ያስፈልጋል፡፡እንደ ውሉ ሳይፈጸሙ የቀሩ አብዛኛው የአስተዳደር ውሎች ችግርም የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ውል ከመግባት ባለፈ ማድረግ የሚገባቸውን ባለማወቅ ወይም ተገቢው ትኩረት ባለመስጠታቸው የሚፈጠሩ ችግሮች ናቸው፡፡ሁሌም የአስተዳደር መስሪያ ቤትና ተዋዋዩ ወገን ውሉ ላይ ያለውን ግዴታ በማስፈጸም ደረጃ እኩል ያለመሆናቸውን በደንብ በመገንዘብ ተገቢውን ክትትል በማድረግ የሚታዩ ክፍተቶችን ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አግባብ በከተማችን የሚገኘው የአስተዳደር ውሎችን አፈጻጸም ውጤታማ ማድረግ ይዋል ይደር የማይባል ጉዳይ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡